
# የአዲስ ኪዳን መቅድም




## መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ

በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ
መንፈሳዊ ኮሌጅ
የሃይማኖት መምህር
1977 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

## ቁጥር - ፩

የምጽፈውም እንዲህ ነው። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁም ጋር ይሁን" /2ተሰሎ.3.17-18/ ::

## ምዕራፍ 12 የጠባቂነት መልእክታት ፣

እነዚህ ሁለት ወደ ጢሞቴዎስና አንዱ ወደ ቲቶ የተላኩት 3ቱ መልእክታት የጠባቂነት/የኖላዊነት/ መልእክታት እየተባሉ ይጠራሉ ይኸም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት ያለ የአመራር፣ የአጠባበቅ ችሎታ ሊኖራቸው እንደሚገባ፣ ምዕመናኑን እንዴት አድርጎ መጠበቅ እንደሚገባቸው ገልጠው ይናገራሉና ::

ካህን የሚሆን ሁሉ አይፃቱ ምን ዓይነት መሆን እንዲገባው፣ በየተዋረዱም የቤተ ክርስቲያን ጠባቂዎች ሁሉ ምን መሆን እንዳለባቸው ስማቸውን ጳጳሳት ቀሳውስት ዲያቆናት እያለ እየገለጠ ከነግብራቸው ይናገራልና/ 1ጢሞ. 3.1-13 ቲቶ 1.5-9/ ::

ከዚህም ሌላ የክርስቶስን ቤተሰብእ እንዴት አድርጎ መጠበቅ የአጠባበቁን ስልት በቤተሰብ አስተዳደር መስሎ ቤቱን ይህና አድርጎ ሊያስተዳድር የማይችል ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ ሊያስተዳድር አይችልም በማለት ማስረጃ ሰጥቶ ይናገራልና/1ጢሞ.3.1-25/ ::

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ የጠባቂነት መልእክታት የጻፈ ጳውሎስ አይደለም የሚል ክፍል ደግሞ ይገኛል፣ ይኸንም ለማለት ከሚያስረደፍራቸው ምክንያቶች ፣

1. ጳውሎስ የነበር የጻፈ የሠራ በ1ኛው ምዕት ዓመት ሲሆን እንዴት ስለ ቤተ ክርስቲያን ድርጅት ስያሜ ቀደም ብሎ ሊጽፍ ሊገልጥም ቻለ ይኸ የቤተ ክርስቲያን ድርጅት የታወቀው 2ና ከ3 መቶ ዓመት በኋላ ነው፣ የሚል ነው ::

www.ethiopianorthodox.org

1ኛ ጢሞቴዎስ 4.14/ 51 ዓ.ም ጀምሮ በግምት እስከ 68 ዓመት ከክ ርስቶስ በኋላ ያለመለያየቱ የሥራ ረዳት የመከራ ጓዱ ሆኖት በሄደበት አገር አብሮት እየዞረ ቆየ በልዩ ልዩ ሀገሮች መልእክትን እያደዘ ሳይ ደክም በታለም እየተሳከ ጉዳ ግዳጁን ፈጽሟል በመጨረሻ ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾሞ ታ
ክክል የጠጥርያት ሥራን ሲሰራ ደሚጥያኖስ የተባለው ከጠዲ ንጉሥ አስገ ደሉት በሰማዕትነት በግምት በ96 ዓመተ ::

2ኛ. <u>ወዴት፣ መቼ ስለምን ተጻፈች፣</u> ይህች መልእክት የተጻፈችበትን በታ የቀደሙ ሊቃውንት አይስማሙበትም፣ ማለት ጥቂቶች በመቄዶን ያን፣ሌሎች በአቴና፣ ሌሎች ደግሞ በሎዶቂያ ነው
ሁሉ አርግጠኛው የትኛው እንደሆነ ሊታወቅ አይቻልም :: ወደ እውነት የቀረበ የሚባለው በኤፌሶን መጻፉ፣ ነው የተጻፈበትም ዘመን አስቸጋሪ በመሆኑ በግምት በ66 እና በ67 ዓ.ም ነው በማለት ይወስኑታል :: የተጻፈበት ምክንያት ግን ጢሞቴዎስ ከሾመት በታ ደርሶ ብዙ እንቅፋት እንደ አገኘው ኃዘኑን ለቅ ዱስ ጳውሎስ ገለጠለት ኋ/ ቅዱስ ጳውሎስ ለሥራው ረዳት እን ዲሆነው በጠባቡም እንዲጸና ለማድረግ እነዚህን መልእክቶች ጻፍ ለታል :: ይኸንም ከጻፈለት በኋላ እራሱ መጥቶ እንደሚገበኘው ተስፋ ሰጠው/3.14/ በትጋትና በንቃት እንዲሰራ /14.14/ ጤናውን ደግሞ እንዲጠብቅ /5.23/ምንም ቢሆን በሕፃንነትህ የሚንቅህ እንዳይኖር አንተም እንዳታፍር ቢል /4.12/ሊሰ ራው የሚገባውን ዝርዝር ጻፍለታል ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 14 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ የተላከች

1. መቼ፣ ወዴት፣ ስለምን እንደ ተጻፈች፣ ይህች መልእክት የተጻፈበት ጊዜ በመጨረሻ በሮም በታሰረ ጊዜ በግምት በ68 ዓመት ከክርስቶስ በኋላ ነው፣ ይህም በሁለተኛ ጊዜ እሥራቱ በሮም ነው :: ጳውሎስ 2 ጊዜ ታስሯል:- በመጀመሪያ እሥራቱ ነፃ በመውጣት የመፈታት ተስፋ ነበረው ስለዚህ በመጀመሪያ መልእክቱ ላይ ምናልባት ከዚህ ከአንበሳ አፍ ያወጣኝ እንደሆነ ብሎ ጸፎ እናገኘዋለን/2ጢሞ. 4.17/ :: በዚህ በመጨረሻ እሥራቱ ጊዜ ግን የሕይወቱን ጉዞ እንደፈጸመ ሩጫውን እንደጨረሰ ሁሉን እንዳደረገ የሚቀረው ነገር ቢኖር ከእውነተኛው ዋጋ ከፋይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሕይወት አክሊልን ማግኘት እንደሆነ ጽፎ እናገኘዋለን/ጢሞ 4.8/ ::ይህ ሁሉ የሚያመለክተን ከሞቱ ትንሺ ቀደም ብሎ በመጨረሻ ሕይወቱ በዚሁ ዓመተ ምሕረት የጻፈው እንደሆነ ነው ::

እርሱ በችግርና በእሥራት ሳለ ወዳጆች ሁሉ ጥለውት በመሄድ እንዳዘነ ሃይማኖታዊ ልጁ ጢሞቴዎስ በፍጥነት ክረምት ሳይገባ ወይም ሳይሞት እንዲደርስለት የጻፈው በመጨረሻም እስራቱ በሮም ሳለ እንደጻፈው ያስረዳል :: የተጻፈበትም ምክንያት ብዙ መናፍቃን ጢሞቴዎስን እንደሚታወኩት በስማ ጊዜ ምንም በእሥር ቤት ቢሆን ሊታገስ አልቻለምና በማንኛውም ጊዜና በታዝም ማለት እንዳይገባው ተግቶ ነቅቶ እንዲያስተምር፣ የክርስቶስ ወታደር እንደመሆኑ መጠን ጠንክሮ እንዲኖር/2.3/ የተሰጠውን ቃል ኪዳን በትክክል እንዲፈጽም ነው/1-14 / ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 15 ወደ ቲቶ የተላከች፤

1. **ሰውየው፤** ሐዋርያው ቲቶ ቅዱስ ጳውሎስ በጣም ከሚወዳቸው ደቀ መዛሙርት የሥራ ረዳት የመከራም ጓዱ ነበር/ገላትያ 2.3./ ትውልዱ አረማዊ የአንጾኪያ ሰው ነው ፡፡ በቅዱስ ጳውሎስ ሰብከት ስለ አመነ የርሱ እውነተኛ ልጅ ይባላል/ ቲቶ 1.4/ ፡፡ ይኸን ቲቶ የተባለውን ሐዋርያ ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ከአንጾኪያ ወደ ኢየሩሳሌም በ50 ዓ.ም ሲሄድ እናገኘዋለን፤ የቅዱስ ጳውሎስ ተላላኪ ሁኖ በብዙ ቦታዎች ረድቷል በተለይም ወደ ገላትያ ቤተ ክርስቲያን ይመላለስ እንደነበር ቅዱስ ጳውሎስ በገለጠው ቃል ይታወቃል ፡፡
/ገላትያ 2.2/ ፡፡ እንዲሁም ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በመልእክት እንደተመላለሰ የሐዋርያ ተግባሩንም እንደፈጸመ እናገኘዋለን/2. ቆሮ.8.18/ ፡፡

በዚህ በሐዋርያዊ ሥራ ሁሉ የተጋ የነቃ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ በብዙ በኩል ተረድቶ የቀርጤስን ቤተ ክርስቲያን እንዲያስተዳድርለት ኤጲስ ቆጶስነት ሾመው፤ ሕግም ሠርቶ አስቀመጠው /ቲቶ 1.5/ በዚህም በተሾመበት ቦታ በትጋት ሲያስተምር ቆይቶ ሐዋርያዊ ተግባሩን በሚገባ ፈጽሞ ዕድሜ ጠግቦ አርጅቶ እንደሞተ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በሰፊው ያስረዳሉ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

2፭. <u>መ ፪፤ ፴ዔት፤ ስለምን እንደ ተጻፈች፤</u> ይህች መልእክት ከመጀ መሪያ፡ ነጢሞቴዎስ መልእክት ጋር ትገናኛለች ስለዚህ ያች የተ ጻፈችበት ቦታ እንዳልታወቀ ይህችም መልእክት የተጻፈችበት ቦታ በግልጥ አይታወቅም አንዳንድ የትርጓሜ ሊቃውንት የመጀመሪያቱ የጢሞቴዎስ መልእክት እንደ ተጻፈች በዚያው ቦታና በዚያው ዘመን ተጽፋለች ሲሉ ይናገራሉ፤ ይኸች ከሆነ በ67 እና በ68 ዓ.ም መሆኑ ነው ። የተጻፈበትም ምክንያት የቀርጤስ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ ቦታዎች ተቋቁመው በቁጥር በዝተው ቢገኙም ገና ያል ደረጁ [illegible] ገዘፈና ለዚህ ሁሉ መልስ ሰጥቶ እንዲያ ስተዳድርለት መመሪያ ለመስጠት ነው ።

የቀርጤስ ሰዎች ጠባያቸው የከፋ ስማቸው የጠፋ ነበርና መከራ እንዳይበዛበት በመጠበት ጊዜም እንዲታገሥ አስቀድሞ የሰዎቹን ጠባይ ይገልጥለታል/ ቲቶ 1.12/ደግሞም በመካከላቸው ብዙ መናፍቃን ነበሩና ከነርሱ እንዲርቅ ምእመናንንም እንዳይ ስቧቸው የመናፍቃንን ክህደት እየገለጠ ጻፈ/1.10-12/ ከዚህም በኋላ ቀና አሳማው የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ የሆኑትን እየመረጠ እንዲሾም እርሱም በትጋት እንዲጠበቅ ነው/1.5-10/ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 16 ወደ ፊልሞና የተላከች

1. ሰውየው፤ ፊልሞና የተባለው ሰው በቆላስይስ የሚኖር የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን አባል የነበር አንድ ባለጸጋ ሰው ነበር ። ወደ ክርስቶስ ትምህርት የተመለሰው በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ነው/ ፊልሞና 19/ ። በቆላስይስ ከሚገኙት ከክርስቲያን አባሎች በጣም ጥብቅ ክርስቲያን እንደነበር ይገመታል/4—7/ ።

እንደዚሁም ሚስቱ አፍጵፊያና አርኪጳስ የተባለው ልጁ በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ያመኑ ጥሩ ክርስቲያኖች ነበሩ ። ይህ ፊልሞና ደግ ባለጸጋ ስለነበር ማንኛውንም ክርስቲያን በቤቱ እየተቀበለ ያበላ ያጠጣ ያሳድርም ነበር ። ቅዱስ ጳውሎስ ማረፊያ የሚሆነው ጎጆ እንዲሠራለት እንዲሁ ጻፈለት/22/ ብዙ አገልጋዮች ነበሩት ከብዙዎቹም ውስጥ አንዱ አናሲሞስ የተባለው አገልጋይ ገንዘቡን አጥፍቶ ከድቶት ቅዱስ ጳውሎስ ወዳለበት ሄደ አማላጅ እንዲሆነው ለመነው ቅዱስ ጳውሎስም አናሲሞስ ዐውነተኛ ክርስቲያን መሆኑን ተረድቶ ተለይቶ ከቤቱም እንደወጣ ሊቀር ስላልፈቀደ በርሱና በፊልሞና መካከል ገብቶ ለማስማማት ሲል ይህችን ደብዳቤ ጻፈ ።

2ኛ. ወዴት፤ መቼ ስለምን እንደተጻፈች፤ ይህችን መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈ በመጀመሪያው በሮም ዕሥራቱ በግምት በ63 ዓ.ም ነው፤ የጻፈበትም ምክንያት በጠፋው ገንዘብ ከጌታቸው ጋር ተቀያይሞ እንዳይቀር ስለለመነው ቅዱስ ጳውሎስ ከዛሬ ጀምሮ ለኔም ላንተም ጠቃሚ የሆነውን ወንድሞችንን አንተ ሳታውቀው ላስቀረው አልፈቀድኩም እንዲሁ ወዳንተ ልልከው አንተም እንደ ወንድም እንድትቀበለው ላኩት ። የጠፋውንም ገንዘብ እኔ እከፍላለሁ ይኸንም ማለቴ አንተ ገንዘብ ወዳጅ አለመሆንህን እየገለጥኩ ነው በማለት እለቱን ለማስታረቅ ጻፈ ።

www.ethiopianorthodox.org

3ኛ. <u>የመልእክቲቱ እውነተኛነት፤</u>

ይህች መልእክት በቅዱስ ጳውሎስ እጅ እንደ ተጻፈች ብዙ ምስክር አለ ::

ይኸውም አንደኛ ምስክር የውጭ ነው፤ አግናጥዮስ፤ ኤጵፋጕዮስ፤ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አባቶች በሰፊው ይመሰክራሉ ::

2ኛ. የውስጥ ምስክር ጸሐፊው ጳውሎስ እንደሆነ እየመሰለ ይናገራል :: /፲.፬ [illegible] ይህች መልእክት ከ ቆላስይ[illegible] ጋር በብዙው ትገናኛለች ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 17 ወደ ዕብራዊያን የተላከች፤

1. የተላከላቸው ሰዎች፤ ይኸች መልእክት የተጻፈች ከአይሁድ ውስጥ ክር ስቲያን ለሆኑት አይሁድ እንደሆነ ይገመታል፤ ነገር ግን በየት አገር ለሚሮ/ አይሁድ እንደሆነ መልእክቷንስ ማንእንደሚቀበላት ስም አይጠራም :: የትርጓሚ ሰዎች ግን ያስረዳት የትም ሁኖ እስራኤላዊ የሆኑው ሁሉ እንዲያነበው ነው፤ በተለይም የሙሴን ሕግ የቤተ መቅደሱን አገልግሎት ጠንቅቀው ለሚያውቁት እንዲሁም የነገሥታቱን የመሳፍንቱን ወደና ታሪክ ጠንቅቀው ለሚያውቁ ሁሉ የተጻፈች ናት :: የሆነው ሁኖ በ3ቱ አገሮች ላሉት ያሁዲዎች ብቻ ይሰጣሉ ፤

   1ኛ. በኢየሩሳሌም

   2ኛ. በኢጣሊያ

   3ኛ. በእስክንድርያ ለሚገኙ ይሁዲዎች፤ ምክንያቱም በነዚህ ሀገሮች ዕብራዊያን በጣም በዛተው ይገኙ ነበርና ::

2ኛ. ጸሐፊው፤ ለማን ተጻፈ ከሚለው ይልቅ ማን ጻፈው የሚለው ጥያቄ ከባድ ሁኖ ይገኛል፤ ምክንያቱም ቅዱስ ጳውሎስ ጻፈው እንዳይባል 1ኛ ኃይለ ቃሉ ከሌሎች መልእክቶች ፈጽሞ የተለየ ሁኖ ይገኛል፤ 2ኛ የጠዲሱን ብቻ ሳይሆን የኦሪቱንም ስርዓት እያነጻፀረ ይጽፈልና :: ቅዱስ ጳውሎስ መምሕረ ሐዲስ ወይም መምህር አሕዛብ የተባለው ይኸን ባልጻፈም ነበርና ::

3ኛ. ጳውሎስ ሁል ጊዜ ሲጽፍ በመጀመሪያም በመጨረሻም በመካከልም ስሙን ይጠራ ነበር፤ በዚህ መልእክት ግን በአንደኛው ቦታ እንኳን ስሙን ሳይነሣ በመቅረቱ ከዚህም የበለጠ ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረኝ ሳይኖር በክርስቶስ መምህርነት አመንኩ ይል የነበር በዚህ መልእክቱ ግን ኮሰሙት የተማርኩ ይላል /2.3/ስለዚህ የጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ አይደለም የማለት አስ ተያየት ይ[illegible] ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 18 የያዕቆብ አጠቃላይ መልእክት

1. ጸሐፊው፤ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ያዕቆብ የሚባሉ ሰዎች ይገኛሉ ከሪዚህም ውስጥ የትኛው ያዕቆብ እንደጻፈት አስቸጋሪ ነው ። እነዚህም ያዕቆብ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፤

   ሀ. ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ የወንጌላዊው የዮሐንስ ወንድም፤ እርሱም ከ12ቱ ሐዋርያት ውስጥ የሚሆን ነው ። ይኸም ያዕቆብ በአንቲጳስ ሔሮድስ /በ44 ወይም በ43 ዓ.ም /በሰማዕትነት ያረፈ ነው ።

   ለ. ያዕቆብ ወደ እልፍዮስ የተባለው ነው፤ እርሱም ከ12ቱ ሐዋርያት ውስጥ የሚሆን ነው ። እልፍዮስ በሚለው ወልደ ተለዩጽም ይለዋል፤ ግን ቀዩለስ የሚለው ወደ ሌላ ቋንቋ ሲወሰድ ነው እንጂ እልፍዮስ እንደሆነ የታወቀ ነው ።

   ሐ. ያዕቆብ የሐዋርያው የይሁዳ ወይም የታዲዎስ ልጅ ነው

   መ. ያዕቆብ የጌታ ወንድም የተባለው ያዕቆብ ይገኛል ። እንግዲህ ከነዚህ ውስጥ ይኸኛው ያዕቆብ ይኸችን መልእክት ጻፍ ይሆናል የሚል ግምት ለመስጠት የሚያስችል አስረጂ የለም፤ ይሁን እንጂ የመጀመሪያው ያዕቆብ ይኸችን መልእክት እንዳልጻፋት ግልጥ የሆኑ ማስረጃዎች አሉን ይኸውም

   1. ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ቀደም ብሎ በ44 ዓ.ም በሰማዕትነት በአንቲጳስ ሔሮድስ ስለሞተ/የሐ. ሥራ 12.2/መልእክቱ ደግሞ ቆይታ የተጻፈች መሆኗ ግልጥ ስለሆነ እርሱ እንዳልጻፋት ግልጥ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

2. የቤተ ክርስቲያን ምስጢራትን አገልግሎት ስለምትናገር ይኸም የሆነው በጣም ዘግይቶ ስለሆነ ያዕቆብ ግን ቀደም ብሎ ስለሞተ እንደልደፋት ሉሳው ማስረጃ ነው ::

2ኛው ያዕቆብም እንዳለጻፈት ግልጥ የሆኑ አስረጅዎች አሉ ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው ይኸ ጦማር ያ ከጸራቅሊጦስ በዐል በኋላ የት እንደነበረ፤ ምን እንደሠራ እስከ መቼ እንደቆየ የጠ.ሥራ እንኳን አልገለጠልንም ። ስለዚህ የት ሆኖ፤ መቼ እንዴት ጻፈው ለማለት ግምትም ለመስጠት አስቸጋሪ ነውና ::

3ኛው ያዕቆብም ይኸኑ የመሰለ ችግር እንዳለበት ስለሚያውቅ መልእክ ግን እርሱ እንገልጻቸን [illegible] ሊሆን ነው፤ እንግዲህ ሆነም ቀረም የጌታ ወንድም እየተባለ ለሚጠራው ያዕቆብ ይሰጥዋል ማለት ነው፤ ምክንያቱም በመልእክቱ ውስጥ እርሱን የሚመለከቱ ብዙ መልክቶች ይገኛሉና ::

የጌታ ወንድም ያዕቆብ እንደጻፈት የሚገመት ከሆነ፤ የጌታ ወንድም ስለሚለው ቃል እንመራምራለን :: የጌታ ወንድም ወይም የጌታ ወንድሞች እየተባሉ የሚጠሩ ሌሎችም ይገኛሉ፤ እነዚህም የያዕቆብ ወንድሞች ናቸው :: ጌታ ከቅ.ማርያም በድንግልና ብቻውን የተወለደ ነው፤ ስለዚህም ከአብም ያለ እናት ከቅድስት ሚርያም ያለ አባት የተወለደ ብቻውን ልዱ "ወልድ ዋህድ" የሚባል እርሱ ሲሆን እንዴት ወንድሞቹ ይባላሉ /ማቴ 13.55/ የሚል አስተያየት ይገኛል፤ ነገሩም ያስኛል፤ ስለዚህም የሚከተለውን አስረጅ እንመልከት ::
ወንጌላዊው እውነተኛ ሲሆን የሚጽፈውም እውነተኛ መሆን አለ ባት፤ ስለዚህ ለምን ወንድሞቹ አለ? የሚል ጥያቄ ይገኛል ሊቃውንት ግን ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ብዙ ምርምር ያደርጋሉ፤ ከብዙዎቹም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ::

www.ethiopianorthodox.org

1. የጌታ ወንድሞች የሚባሉ የዮሴፍ ልጆች ናቸው ዮሴፍ ቅድስት ማርያምን በእጮኛነት ከመውሰዱ በፊት ሌላ ሚስት አግብቶ ስለ ነበር ከርሷ የተወለዱ ናቸው፤ እንግዲህ በአባታቸው በዮሴፍ ምክንያት ከጌታ ጋር በለኖሩ፤ ያዕቆብ ሕፃን እንደመሆኑ ከጌታ ያልተለየ ነበርና ልጆቹ ለጌታ እንደወንድም ሁነው አብረው አደግዋልና ወንድም ወይም ወንድሞቹ ይባላሉ ።

2. የቀደመችው የዮሴፍ ሚስት የነበረችው የቅድስት ማርያም እህት ነበረች እሷ ስለሞተች ልጆችን ቅድስት ማርያም አሳድጋቸዋለች ስለዚህ የጌታ ወንድም አለ ።

ሀ. ከጌታ ጋር አብረው በማደጋቸው፤

ለ. የአክስታቸው ልጅ ስለሆኑ ወንድም ወንድሞች ይባላሉ ነበርና የጌታ ወንድም አለ ። በዚህ ዓይነት የረቀቀም የጎላም ማስረጃ አሁንም በመስጠት ላይ ናቸው ።

እነዚህ የጌታ ወንድሞች የተባሉት ከጌታ ጋር አየኖሩ ለብዙ ዘመናት አላመኑበትም ነበር ፡ዮሐ.7.5/ ። እንዲያውም በርሱ ላይ በተቃራኒነት ይገኙ ነበር/ማር.3.21/

ይኸ ያዕቆብ ግን ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ያመነ ይመስላል፤ እንዲያውም ጌታ ሲነሣ ራሱ የተገኘ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ በሰፊው ያስረዳል/ 1ኛቆ 15.7/ የመንፈስ ቅዱስ ተስፋን ግን ከሌሎች ሐዋርያት ጋር አብሮ የተቀበለ ለመሆኑ ቅዱስ ሉቃስ ይመሰክራል /የሐ.ሥራ.1.14/ ። ቅዱስ ጳውሎስ በተአምራት ተለወጠ በክርስ. ክምና ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ ያዕቆብ በኢየሩሳሌም ላይ ታላቅ በታ ኑሮት፤ ኤጴስ ቆጶስነት ተሹሞ አግኝቶታል/ገላት 18–19/ ። ከ50 ዓመተ ምህርት በኋላ ያዕቆብን የሐዋርያት የመጀመሪያው ሲኖዶስ ሰብሳቢ/ሊቀመን [illegible] 15.13/ ።

www.ethiopianorthodox.org

2. <u>የተጻፈላቸው ሰዎች፦</u> እነዚህ የሚጻፍላቸው ሰዎች በመጀመሪያው መልእክቱ በግልጥ በ2ኛው መልእክቱ ግን በተዘዋዋሪ መንገድ እነማን እንደሆኑ ይነገረናል ። በ2ኛው መልእክቱ 2ኛ ጊዜ ጻፍኩባችሁ ሲል ለነዚያው መጻፉን ይጠይቃል ። በመጀመሪያው መልእክቱ ግን በክርስቶስ ስሙ ለተበተኑ በጳንጦስ በገላትያ በቀጰዶቅያ በእስያ በቢታንያ /1.ጴጥ.፩፡1/እያለ ይገልጽልናል ። ይኸም መልእክት ለነዚህ ብቻ ሳይሆን በጠቅላይ ለክርስቲያን ሁሉ መሆኑን ያመለክታል፤ ምክንያቱም በክርስቶስ አምነው ለተበተኑ ሁሉ ነውና ። ከዚህም የተነሣ መልእክቶቹ አጠቃላይ መልእክቶች ተብለው ሊሰጠሙ ቻሉ ። የትርጓሜ ሊቃውንት ግን እነዚህ ሰዎች በሥጋ እሥራኤል የተባሉ አይደሉም በመንፈስ እንጂ በዓለም ለተበታተኑት በመንፈስ እሥራኤላዊያን ለሆኑ ክርስቲያን ሁሉ የተላኩ ናት ።

3. <u>መቼ ተጻፈች ይጴጥሮስ መልእክታት፤</u> መቼ እንደ ተጻፈች የሚያመለክት ነገር የለም ግን ስልዋኖስንና ማርቆስን ስለሚያነሣ ምናልባት እነዚህን ሰዎች ከጳውሎስ ዕረፍት በኋላ አግኝቷቸው እንደሆነ በማለት ከ67 እና ከሰልሣ ስምንት ዓ.ም በኋላ እንደ ተጻፈ ይገምታል ።

ምክንያቱም ጳውሎስ እያለ ቢሆን ኖሮ እነዚህ ሰዎች ከርሱ አልተለዩም ነበር ሊሆን አይችልም በማለት ነው ።

<u>ሀ. የመጀመሪያ የጴጥሮስ አጠቃላይ መልእክት፤</u>

ይኸችን መልእክት ጴጥሮስ በታናሽ እስያ ለሚገኙ ሕዝቦች በመጻፍ እንዴት ጴጥሮስ የግዝረት ሰዎች መምህር ሲሆን ለቶፋን ክርስቲያኖች ጻፈ ።

## ለ. 2ኛ ቀ የጴጥሮስ አጠቃላይ መልእክት፤

ይኸች መልእክት የተጻፈችበትን ቦታ የሚጠቁም ምንም ነገር የለም ምናልባትም የመጀመሪያይቱ መልእክት ለተጻፈችበት አገር ተጽፋ ይሆናል ። የተላከችላቸው ሰዎች ግን እነዚያው መሆኑን በዚህች መልእክት በ3ኛው ምዕራፍ በቁ. 1 ይገለጣል ። በመጀመሪያ ምዕራፍ በቁጥር 1 እንደሚገለጠው ግን የሚላኩላቸው ሰዎች በዚ ላሉ አብያተ ክርስቲያን/ላል ተወሰኑ/ በእምነት ከፍ ያለ አስተያየት ላላቸው፤ ለጸጋው አቀባበል በቂ ለሆኑ ከነጴጥሮስ ጋር እኩል ለሆኑ እንደሆነ ያመለክታል ። ከሌሎች ለይቶ ይኸችን መልእክት አጠቃላይ የሚያሰኛት እንደዚህ አይነቱ የጠቅላላነት ቅጥር ነው ።

ይኸችን 2ኛ መልእክት ለመጻፍ ያስፈለገበት ምክንያት በዚያ የሚገኙትን ክርስቲያኖችን ሁሉ ከልዩ ልዩ አደጋ ለመጠበቅ ነው፤ ምክንያቱም ከአማንያኑ መካከል የሐሰት መምህራን እየተነሱ ያውኳቸው ነበርና ።

ከመጀመሪያው መልእክት በብዙ መልክ ለየት ትላለች የመጀመሪያው በስደትና በልዩ ልዩ መከራ ይገኙ ስለነበር ከዚያም ለመጽናናት ተጻፈች ይኸችን ግን በሐሰት ወንጌልን እናስተምራለን ከሚሉ ከዮዱ ጠሰዊያን እንዲርቁ እንዲጠነቀቁ መመሪያ ለመስጠት ነው ። ስለዚህም እውነተኛውን ክርስቲያናዊ ትምህርት ብቻ እንዲከተሉ ይገልጽላቸዋል ።/3.1–3/ ። ወደ እውነተኛ ለመምራት እውነትን ለማሳየት/1.5–7/ ተጻፈች ።

www.ethiopianorthodox.org

2. <u>የመልእክቷ እውነተኛነት፣</u> ይኸችን መልእክት ለቅዱስ ጴጥሮስለመስጠት ብዙዎች አይስማሙም በመጀመሪያው ጊዜ ብዙ ክርክር ነበረባት፣ ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተባሉ የጴጥሮስ ናት ብለው በጽሑፍ ስለመሰከሩ የጴጥሮስ መልእክት እየተባለች ተጠራለች የሮማ ቀሌምንጦስ፣ ሔርማስ፣ ሰማዕቱ ዩስቲኖስ፣ ሔሬኒያስ የአስክንድርያው ቀሌምንጦስም የጴጥሮስ መልእክት እንደሆነች መሰከረ ዋል :: እንዲያውም በመጀመሪያው ጊዜ የጴጥሮስ መልእክት እንደ ሆነች ጽፎ የመሰከረ አርጌኒስ ነው ::

በክርክሩም ምክንያት ይኸች መልእክት ከአንዳንድ ከዴክስ ላይ አትገኝም፣ ለምሳሌ ከሙራቶሪዮ ቀኖና አትገኝም :: ከሶርያዊ ትርጉም ከፔሽታ ላይ፣ ከጥንታዊ ላቲን ትርጉም ላይም አትገኝም :: የውስጥ ምስክሯ ግን በጣም ደካም ያለ ነው፣ ይሁን እንጂ ሰንደኛ በመጀመሪያ ላይ ከስምዖን ጴጥሮስ የተላከች ይላል/1.1/ ቀጥሎም በደብረ ታቦር ተገኝቶ የክርስቶስን ራእይ መለወጥ ያየ እንደሆነ ይናገራል/1.16—18/ ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 20 የዮሐንስ አጠቃላይ መልእክታት

በዮሐንስ ስም የቀረበትን ሦስቱ መልእክቶች የጻፈ አራተኛውን ወንጌል የጻፈ ሐዋርያው ዮሐንስ ነው። የዮሐንስ መልእክታትም እንደሆኑ የሚያስገምታቸው 3ቱም መልእክታት ተመሳሳይ ሁነው ከዮሐንስ ወንጌል ጋር አንድ ዓይነት አገላለጥ ስላላቸው ነው። የጸሐፊውን ስም ግን ማን እንደሆነ በውስጣቸው የሚገለጥ አንቀጽ የለም ። ከ2 ላይ ብቻ የጸሐፊውን ማዕረግ ሽማግሌው ሲል ይገልጣል/2. ዮሐ.1.3. ዮሐ.1/ ።

እነዚህ 3ቱ መልእክቶች በጣም ዘግይተው እንደቀረቡ ይነገራል፤ ይሁን እንጂ የዮሐንስ መልእክቶች እንዲሆኑ የጥንት አበናት አምነው ተቀብለዋቸዋል፤ በተለይም የመጀመሪያይቱን መልእክት ።

የመጀመሪያይቱ መልእክት ከ4ተኛው ወንጌል ጋር በፍጹም ተመሳሳይ ናት፤ እንደገናም ሁለቱ መልእክቶች ከመጀመሪያይቱ መልእክት ጋር ግንኙነት ስላላቸው ሁሉም የዮሐንስ እንደሆኑ ያረጋግጣሉ ።

2. <u>የተላከላቸው ሰዎች፤</u> ሀ. ይኸች የመጀመሪያዪቱ መልእክቱ ለግል ሰው ወይም ለማኅበር/ለቤተ ክርስቲያን/ ተልካ እደሆነ ግልጥ የሆነ ማስረጃ የላትም ። አውግስጢኖስ የተባለው አባት ለፋርስ /ፖርቲስ/ ሰዎች እንደተላከች ይናገራል ። ሌሎች ሊቃውንት ሲተረጉሙ ግን ዮሐንስ ድንግል ንጹሕ ነበር፤ ስለዚህ በግሪክኛ ፖርቴኖስ ማለት ድንግል ለማለት የተጻፈውን በማየት ፖርቲስ ብሎ ሊጽፍ ቻለ ፔርስያ ማለት እንደሆነ የዓመቱ ሊቃውንት ለፍርስ ይሰጣሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህች መልእክት የብሉይ ኪዳን ጥቅስ በአንድ ቦታ እንኳን ሳይ ገለጥ ይገኛል፤ ይኸም መጽሐፍ ለአረማውያን እንደ ተጻፈች የሚያስረዳ ነው ። የዚህ አስተሳሰብ ዮሐንስ በኤፌሶን የመጨረሻ ጊዜውን ያሳለፈ ስለ ነበረ እንቲፖቲኩ አሲያ/ የአንቲፖስ ግዛት በሆነው ሁሉ/ የተላኮች ለሁሉም የምትደርስ መልእክት እንደሆነች ያመለክታል ።

3. <u>የት፤ መቼ፤ ስለምን ተጻፈች?</u> እስከአሁን ድረስ ያየነውን በትክክል የምንቀበለው ስለሆነ ይኸች መልእክት የተጻፈችው በኤፌሶን ነው፤ ጸሐፊውም ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ነው ስለ ዘመኑ ደግሞ በግምት በ96 ዓ.ም እንደሆነ ይነገራል ።

የተጻፈችበት ምክንያት ግን በክርስቲያኖች መካከል ስለ ተነሱት መናፍቃን ነው፤ ይኸውም ግኖስቲኮስ የተባሉትን ሰዎች ኑፋቄ ለማጋለጥ ነው ። እነዚህ መናፍቃን ከቤተ ክርስቲያን ሕግ ወጥተው ማኅበርን አናውጠው ነበርና ጸጥ ለማድረግ ነው ። እነዚህም መናፍቃን በ2ት ዓይነት ኑፋቄ ጸንተው ብዙውን ሕዝብ ያስነክሱ ነበር፤

1. የክርስቶስን አምላክነት ይጠራጠሩ የነበር፤ ይኸውም ሰው ሲሆን አምላክ ሊሆን አይችልም በማለት ኢየሱስ የማርያምና የዮሴፍ ልጅ ነው ይኸም ከሆነ ሩቅ ብእሲ ነው፤ ግን በጥምቀት ጊዜ ክርስቶስ አደረበታል፤ ስለዚህም ታእምራት ያደርጋል ይሉ ነበር ።

በዚህን ጊዜ ዮሐንስ ሊታገስ ስላልቻለ ቃሉን ተግሣጽ ያለበትን ኑፋቄያቸው በመግለጥ ሐሰተኞች የክርስቶስ ተቃዋሚያች እያለ ጻፈ/1.1–4፤2.22፤ 23.4.2–3፤5.5–6/ ።

www.ethiopianorthodox.org

2ኛው ደግሞ ክርስቶስን እንደ ኃጢአተኛ ይቆጥሩት ነበር፤ ማለት ሰው ከሆነ ከኃጢአት የሚርቅ የለምና ክርስቶስ ኃጢአተኛ ነው የሚሉ ነበሩ ። ዮሐንስ ስለዚህ መልስ ይሰጣል፤ ማንኛውም ሕግ ወጥ ሁሉ ኃጢአተኛ ነው፤ ኃጢአትም ሕገወጥነት ነው/3.4/ ። ኃጢአተኛው ሁሉ የዲያብሎስ የበኩር ልጅ ነው/3.7/ ክርስቶስ ግን ሕግን የፈጸመ ለሕግም ታዛዥ ሁኖ ስለኃጢአተኞች ተሰልፎ ሞተ ለማለት ጻፈ ። እንኳን ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የሚወለዱ ሁሉ ኃጢአትን አይሰራም ለማለት ጻፈ /1.8-10/ ።

ከነዚህ 2 ኑፋቄዎች የተነሣ ይኸችን መልእክት ለመጻፍ ተገደደ ።

4. <u>የመልእክቷ እውነተኛነት፤</u> መልእክቷ የዮሐንስ እንደሆነች የውስጥ ምስክርነቷ ከወንጌሉ ጋር 1 በመሆኗ ይታወቃል ።

ስለ ውጭ ምስክርነት በመጀመሪያ ፖሊካርፖስ ወደ ፊልጵስዩስ በጻፈው አስረድቷል ሔሬኔዎስም በልዩ ልዩ ጽሑፍ ገልጠ ጽፏል ። አውሳቢዮስም በቤተ ክርስቲያን ታሪኩ 5.8 ላይ ገልጠ ጽፏል የእስክንድርያው ቀሌምንጦስም የዚህች መልእክት ጸሐፊ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደሆነ ገልጠ ጽፏል ።

ለ. <u>2ኛይቱ የዮሐንስ አጠቃላይ መልእክት፤</u>

1. <u>ጸሐፊውና ተቀባዮቹ፤</u> የዚህች መልእክት ጸሐፊ ራሱን ሽማግሌው ይላል/1.1 / ከዚህም ቃል የተነሣ በመተርጐማን ሊቃውንት ዘንድ ብዙ ክርክር አለ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ይኸች መልእክት ከመጀመሪያው መልእክት ጋር ብዙ ግንኙነት ያላት ሁና ትገኛለች ማለት ከቃላቱ በዐረፍተ ነገሩ በምስጢሩ ሁሉ፤ ስለዚህም ከመጀመሪያው መልእክት የቀጠለች ናት በማለት የሚያስችሉ ብዙ ተመሳሳይነት ስላለው ያለ ጥርጥር፤ ያለክርክርም ጸሐፊው ዮሐንስ

www.ethiopianorthodox.org

ወንጌላዊ ነው ለማለት ይቻላል ::

ሌሎች የሚጠራጠሩበት የዮሐንስ ወንጌላዊ አይደለም ሲሉ የሚናገሩበት ምክንያት አለ፤ ይኸውም ፓፒያስ በሰጠው መግለጫ መሠረት በኤፌሶን ሌላ ሽማግሌ ዮሐንስ የተባለ ቄስ እንደነበረ በመግለጡ ሽማግሌው ያለው ያነን ነው በማለት ነው ::

ይኸን የመሰለውን ጡተታ በወንጌሉ ላይ አስፋፍተን የተናገር ነው ስለሆነ ከዚሁ ላይ እንደገመቱም ወንጌሉን የጻፈ ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ መሆኑን ከተቀበልን ይኸቺንም መልእክት ወንጌሉን የጻፈ እንደጻፈት የታወቀ ነው ::

ሌላው የሚያስቸግረው ነገር የመልእክቷ ተቀባይ ነው፤ ጸሐፊው እንደሚለው ለተመረጠች እመቤት ይላል/ ፩.፩. / ይኸን ይዘው ሊቃውንት በአስተያየት ይለያያሉ ፩ኛው ወገን እንዴት የተለየች ዮሐንስ የሚያውቃት ከአረማዊያን ወገን ክርስቲያን የሆነች በነገዷ ትልቅ የሆነች ሴት ትሆናለች፤ የርሷን ክብርና መብት በመጠበቅ ሲጽፍ የተመረጠች እመቤት አለ :: ሌላው አስተያየት የተመረጠች እመቤት የሚላት ቤተ ክርስቲያን በ፩ ዴት ሴት መስሉ ነው የሚሉ አሉ :: ይኸን አስተያየት ብዙዎች የትርጉም ሊቃውንት ይቀበሉታል ::

የኛ ሊቃውንት ግን በተጨማሪ የተመረጠች እምቤት የሚለውን ለቅድስት ማርያም ይሰጣሉ፤ ስለዚህም የቅድስት ማርያም በዓል በሆነ ጊዜ እንዲነበብ ያደርጋሉ ::

2. <u>ወዴት፤ መቼ፤ ስለምን ተጻፈች፤</u> ስለ ጸሐፊቱ ቦታና ዘመን ምንም ፍንጭ አይገኝም አሁንም የምንሰጠው ግምት እንደ፩ኛዋ መልእክት ይተጻፈችበት አገር በኤፌሶን፤ እርሷም እንደ ተጻፈች ነው ይኸውም በ፺፭ ዓ.ም መሆኑ ነው ::

www.ethiopianorthodox.org

ስለ ተጻፈችበት ምክንያት ግን የሚመስለው ዮሐንስ ለሰበከት በተ ዘዋወረበት ጊዜ ስሟ የተገለጠው እምቤት ልጆች የተቀበሉት ያስተናገዱት ያመሰሳለ፣ በለዚህም እናታቸውን ለማመስገን ደብታውን ለመግለጥ የጻፉ የመሰሳለ/ 4/ :: ዲያውም በክርስቲያኖች መካከል መናፍቃን በዝተው እንደሚገኙና እንዲጠነቀቁ ለመጻፍ ምክንያት ሆነው :: ይኸን የመሰለው ምክንያት ለመጀመሪያይቱ መልእክት ተገልጠ ነበር፣ አሁንም መልክቷን ተመሳሳይ ያደረጋት ምክንያት ከዚያች ጋር አንድ ዓይነት ስለሆነ ነው ::

ከዚህም አያይዞ ክርስቲያኖች ሁሉ የኑፋቄ ትምህርት የሚያመጡትን በቤታቸው እንዳይቀበሏቸው ያስጠነቅቋል / 10—11/ :: በመናፍቃን ላይ ጦባድ ቃል በመናገር መልእክቷን ከባድ ያስመስሳታል እንጂ በመጀመሪያዩ መልእክት በለ ፍቅር አስፈፍቶ እንደጻፈ በዚህችም መልእክት ላይ ባለ ፍቅር በጣም አስፋፍቶ ይጽፋል ::

3. <u>የመልእክቲቱ እውነተኛነት፣</u> ስለዚህች መልእክት እውነተኛነት በው ስጡ ስለሚገኘው ምስክርነትና የውጭ ምስክርነት ከመጀመሪያዩ መልእክት የምትለይ አይደለችም ስለዚህ እነዚያው አባቶች ለእ ንደኛዋ መልእክት የመሰከሩ ለዚህችም መስክረዋል በውስጧም የሚ ገኙ ኃይለ ቃል የመጀመሪያውን መልእክት በሰም ተከቶልና በሰም ትመስል ያው ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደጻፈት የታመነ ነው ::

ሐ. <u>3ኛ የዮሐንስ አጠቃላይ መልእክት፣</u>

1. <u>ጸሐፊውና ተቀባዩ፣</u> በ2ኛዋ መልእክት ላይ እኔ ሽማግሌው ሲል ማዕረጉን ገልጦ የጻፈውን ለዮሐንስ ወንጌላዊ ሰጥተን ከተናገ ርን የአሁኑም በዚያው መልክ የገለጠውና በውስጡም ብዙ ተመሳሳይ ቃል፣ ተመሳሳይ ዐረፍተ ነገር ምባጡር ስላለበት ይኸችን 3ኛዋን መልእክትም የጻፈት ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው ::

www.ethiopianorthodox.org

ተቀባዩ ግን አንድ ጋይዮስ የተባለው ምእመን ነው፤ ይኸ ስም ግን በዚያን ጊዜ በሮማውያን ዘንድ በጣም የተለመደና የወል የሆነ ስም ነበር ። በቅዱስ ጳውሎስ መልእክቶችም 3 ጋይዮሶች ተገልጠው እናገኛለን፤ ከነርሱም

1. ጋይዮስ መቄዶንያዊ፤ ከጳውሎስ አብሮት የሄደ ነው/የሐ.ሥራ. 20.4/ ።

3ኛው ደግሞ የቆሮንቶስ ሰው ነው፤ ለጳውሎስ መስተንግዶ ብዙ ጊዜ ያቀረበ/ሮሜ 16.23 1 ቆሮ 1. 14/ ። ምናልባት ይኸ የመጨረሻ መሆን አለበት መልእክቱ የተጻፈችለት፤ ምክንያቱም ስለ እንግዳ ተቀባይነቱ ይገልጥልና ።

2. <u>ወዴ፤ መቼ፤ ስለምን ተጻፈች?</u> እንደመጀመሪያው መልእክት ይኸችም 3ኛዋ/ በኤፌሶን በ96 ዓ.ም እንደተጻፈች አበቶች ይገምታሉ ።

ስለተጻፈችበት ምክንያት ግን ዲዮጥራጢስ የተባለ የክርስቲያን ጠላት ተነሥቶ ወንጌላዊያን ይቃርም የክርስቶስም ስም እንዳይጠራ ይሰበብ ነበር፤ በዚህ አንፃር ደግሞ ጋይዮስ የወንጌል መልእክቶች የሆኑትን ሁሉ ያከበር እየተቀበለ እያስተናገደ ያሳድርም ስለነበር ይኸን ከወንጌላዊያን ውስጥ አንዱ ለዮሐንስ ነግሮታል፤ ስለዚህ ጋዮስን ለማመስገን ዲዮጥራጢስን ለመውቀስና ብዙ መጥፎ ሥራውን ለማጋለጥ አጭር የሆነች ይኸችን መልእክት ላከ /10/ ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በጣም ትንሿ መጽሐፍ ይኸች መልእክት ናት ።

www.ethiopianorthodox.org

3. <u>እውነተኛነቱ፤</u> ስለዚህች መልእክት እውነተኝነት ለ2ኛዋ መልእክቱ የመሰከረ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እነአውሳብዮስ እና ኦሪጌኒስ ሌሎቹም እንዲሁ መስከረዋል፤ ጴጥሮስ እንደጻፋት በውስጥ ምስክር ደግሞ የቀደሙትን 2ቱን መልእክት መስሎ አክሎ ስለምትገኝ ጴጥሮስ ወንጌላዊ እንደጻፈት የታመነ ሆኖ ይኖራል ።

www.ethiopianorthodox.org

/ቆሮ. 9.5/ በሉ ወንጌላዊ ሥራው የት እንደሠራ፣ እስከመቼ እንደቆየ ምንም ፍንጭ አለተገኘም ኤጊሉፖስ የተባለ ታሪክ ጸሐፊ ብቻ እንዲህ አድርጐ ሲተርክለት ይገኛል፣ የርሱ የልጅ ልጆች ገበሬዎች ነበሩ፣ የንጉሡ የዳዊ ዘመድ ተብለው ተከሰሱ ወደ ንጉሡ ነገሥቱ ወደ ደሚቲያኖስር ቀረቡ ፣ የዳዊት ዘር ከሆኑም የዳዊትን መንበር መንግሥት በመፈለግ በሕዝብ ዘንድ ሁከትን ይፈጥሩብናል ብሎ በመፍራት ነው ። ይኸ ንጉሠ ነገሥት [illegible] ጊዜያት በኋላ [illegible] /አውሳ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 3.19/ ።

2. <u>የመልእክቱ ተቀባዮች፣</u> መልእክቱን የሚቀበሉት ሕዝቦች እነማን እንደሆኑ ምንም የሚያስረዳ ነገር አልተገኘም፣ ግምት እንኳን ለመስጠት የሚያስችል ነገር የለም ። ራሱ ግን ሲጠራቸው "ለተጠራችሁ በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠበቃችሁ ሁሉ" ሲል ይገልጣል/1/ እነዚህም በቅድስትና እንዲኖሩ በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ ይመክራቸዋል/20/ ምናልባት እነዚህ ክርስቲያኖች ከአይሁድ ዘንድ የተመለሱ ሊሆኑ ይችላሉ ።

3. <u>ወዴት፣ መቼ፣ ስለምን ተጻፈች፣</u> ይህች መልእክት የተጻፈችበት ቦታ ግልጥ አይደለም፣ አይታወቅም በለዘመኑ ግን ከጴጥሮስ 2ኛ መልእክት ጋር የምትገናኝበት ብዙ ነገር ስላለ እርሷ በተጻፈችበት ጊዜ የተጻፈች ሲሆን ትችላለች የሚል ግምት አለ እርሱም በ66 ዓ.ም ገደማ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

መልእክቷ የተጻፈችበትን ምክንያት አንድ ከባድ አደጋ በክርስቲያኖች ላይ ደርሶ ከምግባር ከሃይማኖት አንዳንዱ እንደ ተናወጡ ሰምቶ በታላቅ ኀዘን ክርስቲያኖች በክርስቶስ የሚገኘው ሕይወት እውነተኛ እንደሆነ ስለዚህ በእምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ ለማስተማር ነው ። በክርስቲያኖች መካከል ሐሰተኞች መምህራን ተነስተው ክርስቲያኖችን በአስቸገሯቸው ጊዜ ዮሐንስ ሐሰተኞችን ለማጋለጥ ክርስቲያኖችን ጸጥ ለማድረግ እንደጻፈ ይሁዳም ሐሰተኞች መምህራንን ለማጋለጥ እውነተኞች ክርስቲያኖችን በተማረት ትምህርት በተሠራላቸው ሥርዓት ጸንተው እንዲኖሩ ለማስተማር ነው ።

በዚህች ትንሽ መልእክት ይሁዳ ጠቃሚ ትምህርት ለመስጠት በቂ አድርጓታል እውነተኛዋንም እምነት ክርስቲያኖች እንዲጠብቁ ሐሰተኞች መምህራንን እንዲርቁ ለመግለጥ ቢል ጻፈ /3 / የመናፍቃኑን ሥራና ትምህርት ገልጦ በመንቀፍ ይኸን የሠሩ ለዘላለም ቅጣት እንዳለበት በመግለጥ ጻፈ /5—7.16/ ። ኃጢአተኞች ባለመመለሳቸው እንደሚቀጡ የተመለሱት እንደሚድኑ የሔኖክን ዘመን በማጥቀስ ጻፈ /14—19/ ። በቅድስት እምነታቸው እንደ ታነጹ ከቢደላቸው እንዲመሰሉ ጻፈ / 20 / ።

4. <u>የመልእክቷ እውነተኛነት፤</u> ይሁዳ የያዕቆብ ወንድም እንደጻፈት የሚመ ምስክር ብዙ አሉ፤ ለምሳሌ ፖሊካርፖስ ወደፊልጰስዩስ በላከው መልእክቱ የእስክንድርያ ቀሌምንጦስ፣ አውሳብዮስ /ቤተ ክርስቲያን ታሪክ 2.23/ ከዚህም ጋር በሙራቶሪ የቀኖና ላይ ትገኛለች ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 21 የይሁዳ አጠቃላይ መልእክት

1. ጸሐፊው፤ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ይሁዳ በሚል ስያሜ ሰባት ሰዎች ይገኛሉ ይኸውም ሚያስየው በአይሁድ ዘንድ የተለመደና ብዙ ሰዎች ይጠሩበት እንደነበር የሚያመለክት ነው ::

ከነዚህ ከሰባቱ ይሁዳዎች 2ቱ ይኸችን መልእክት እን ደጻፉ ይገመታል፤ እነርሱም ከ12 ሐዋርያት አንዱ የያዕቆብ ወንድም የሚባለው ይሁዳ/ ሉቃ. 6. 16/ :: በዚህ መጽሐፍ ግን ወንድም ልጅ ሳለይ ይሁዳ የያቆብ ይሳል፤ ምናልባት ግን ለጡ ሰዐዐን አይ ቀርም የሚል ግምት አለ ::

2. ይሁዳ የጌታ ወንድም/ ማቴ. 13.55. ማር. 6.3/

ከነዚህ ከ2ቱ ይሁዳዎች የመጨረሻው ይሁዳ ይኸችን መል እክት እንደጻፈት በበለጠ ይገመታል፤ ምክንያቱም ይሁዳ የያዕቆብ ብሎ ራሱ ስለሚናገር ነው /1 / ከዚህም በ ቀር የርሱ አይደለም ብሎ የተነሣ ተከራካሪ የለምና የጌታ ወንድም ስለሚለው በያዕቆብ መልእክት ያተት ነው ስለሆነ መለበ ፍለን ወዲያ እንመለከት፤ ከርሱ ጋር አንድ ነውና :: ይህ ይሁዳ እንደሌሎች ወንድሞች ከትንሣኤ በፊት በክርስትና አላመነም ነበር /ዮሐ. 7.3–8 ፤ የሐ. ሥራ. 1.11/ :: ኑሮውም ባለሚስት ነበር ወይ ሐዋርያዊ ተግባርም ሲሔድ ከሚስቱ ጋር አብሮ ይሔድ የነበር ይመስላል፤ ምክንያቱም ጳውሎስ ለ ተሰበሰቡት የመልስ አስረጅ አርጉየሚያቀርበው የይሁዳንና የወንድ ሞቹን ሚስት ይዞ መዞርን ነውና ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 22 ራእዩ ዮሐንስ

1. ጸሐፊው ፤ ከጥንት ጀምሮ እስከ 19ኛው ምዕተ ዓመት የተነሱት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሊቃውንት ሁሉ ይህ መጽሐፍ በዮሐንስ ወንጌላዊ እጅ እንደ ተጻፈ በአንድ ድምፅ መስከረዋል ::

ይኸውም መጽሐፍ ራሱ በውስጡ 4 ጊዜ ... ስያለ በለሚጠራ ነው/ 1.1፤4፤9.2/2.8/ ይኸም ዮሐንስ ወንጌላዊ መሆኑን ያረጋግጣል :: ነገር ግን ቀጥሎን የክርስቶስ ባሪያ በለሚል ይኸም ዓይነት አገላለጥ በዮሐንስ ... ሁኑ ጥርጣሬን ሊያመጣ ቸሏል :: ከዚህም ጋር በጽሑፍም በቃል አገባቡም በምሥጥሩም ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ጻፈው የሚያስኙ ነገሮች አይገኙበትም ምክንያቱም ከወንጌሉ ፈጽሞ የተለየ አገላለጥ አለውና :: 2ቱን መጻሕፍት ሲያነጻጽራቸው 2ቱም መጻሕፍት የዚያው የአንድ ሰው ጽሑፎች ናቸው ለማለት አያስችሉም :: ይሁን እንጂ የክርስቶስ ባሪያ ሲልም ባለሟልነቱን ታማኝ አገልጋይነቱን የሚገልጥ መሆኑን እንጂ ሌላ አሳብ የሚያመጣ አይደለም፤ ስለዚህ ይኸን ራእይ የተባለ መጽሐፍ የጻፈ ማን እንደሆነ ብዙ ውይይት ሆኗል :: ነፃ አስተሳሰብ ያላቸው ወንጌሉን ለሌላ ዮሐንስ ሰጥተው ይኸንን ራእይ የተባለ መጽሐፍ ለዘብዴዎስ ልጅ ለወንጌላዊ ዮሐንስ ያደርጉታል፤ አርቶዶክስ አስተያየት ያላቸው ሊቃውንት ግን ወንጌሉን ለዮሐንስ ወንጌላዊ ሰጥተው በተጨማሪም ራእዩንም እርሱው እንደጻፈ ይናገራሉ :: ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደጻፈው የሚመሰክሩት ውስጥ አንደኛው ሔሬኔዎስ የተባለው አባት ነው/ለመናፍቃን መልስ በተጻፈው በ5.30.3/ እርሱም እንዲህ ሲል ይገልጣል የዮሐንስ ራእይ ከደሚጥያኖስ በኋላ ብዙ ሳይቆይ ዮሐንስ አያት ጻፉትም ይላል፤ ይኸም ሆነ በ96 ዓ.ም ጻፈት ማለት ነው ::

www.ethiopianorthodox.org

አውሳቢዮስም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በ318.4 ላይ ዶሚቲያኖስ ብዙ ክርስቲያኖችን አግዟል አሰድዷል በሃይማኖታቸው ምክንያት በዚህም ሳቢያ አክስቱን ፍላቪያስ ፊኒቲላስ የተባለችውን ሳይቀር አግዟት ነበር ።

ይኸ ሁሉ የክርስቲያን ስደት በሰባቱ አብያት ክርስቲያን ሁሉ እንደሆነ የታወቀ ነው/ራእ.2—3 ምዕ/ ።

2ኛው አስተያየት ደግሞ መጽሐፉን ከኔሮን ስደት ጋር እያያዘው የሚናገሩ አሉ እነርሱም ራእይ የተጻፈው ከኔሮን ሞት በኋላ ትንሽ ቆይቶ ነው፣ ይላሉ ይኸም ማለት በ68—69 ገደማ መሆኑ ነው ።

ይሁን እንጂ ይኸ መጽሐፍ በዮሐንስ ወንጌላዊ እንደተጻፈ ጌታም እንዳዘዘው ራሱ ዮሐንስ ገልጦ ጽፏል /1. 10—11/ ። ይኸም መጽሐፍ ለተወሰኑ አብያተ ክርስቲያን ተጻፈ የነርሱን ጉድለት ለማረም በተለይም የአንቲጳስ ግዛት በነበረው አገር በታናሽ እስያ ይገኙ ስለነበሩት የቱ አብያተ ክርስቲያን ነው ። /1.4 /እነርሱም ኤፌሶን አዝሚርኒ፣ ፔርጋሞን ቲያጥሮን ሰርዲስ ፣ ፊልደልፍያስ፣ ላኦዲቅያስ የተባሉት ናቸው ለነዚህ አብያተ ክርስቲያን አለቆች ተላከ ። እነዚህም በጌታ ዘንድ የቤተ ክርስቲያን መላእክት የተባሉ ናቸው ። 7 ብሎ የተናገረው ግን ፍጽምነትን ለመግለጥ እንጂ ለነዚህ ብቻ የተጻፈ አለነበረም 7 ሁልጊዜ ፍጽም ነውና ። በለዚህ ለዓለም አብያት ክርስቲያን በጠቅላላ የተላከ መጽሐፍ ነው ። የዚያን ጊዜም የአሁኑም ሕዝብ ሊያውቀው ሊጠብቀውም እንደሚገባ አውቆ ያስተላለፈው ጽሑፍ ነው ። ከጰንጤቆስጤ ጊዜ ጀምሮ እስከ ጌታ መምጣት ድረስ ቤተ ክርስቲያን ጸድታ እንድትገኝ በዓለም ያሉ የቤተ ክርስቲያን አለቃ የሆኑ ሁሉ ታጥቀው ተጠንቅቀው እንዲሠሩ የሚያመለክት ትምህርት ያለበት ራእይ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

2. <u>የትርጓሜው ስልት</u>

የዮሐንስ ራእይ ትርጉም የማይረዳ አስቸጋሪ ነው፤ ስለዚህ ይኸን ለመተርጎም ልዩ ልዩ ስልቶች ተገለጡ እነርሱም 4 ናቸው ::

ሀ. <u>አሊጎሪክ ስልት /የስምት ትርጉም/</u>በዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አባቶች እንደቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያና እንደ አርጌንስ ያሉት ናቸው እነዚህ ሰዎች በጠቅላላ ቅዱስ መጽሐፍን ለመተርጎም በዚህ ስልት የተጠቀሙ ይኸንም ለማድረግ የተገደዱበት የሺህ ዓመት የክርስቶስ ንግሥነት የሚለውን አስተሳሰብ ለማፍረስ ነው ::

ለ. <u>ታሪካዊ ትርጉም፤</u> በዚህ ስልት የሔድን እንደሆነ ደግሞ በዚህ መጽሐፍ የተጻፈው ሁሉ ለአሁኑ ዘመን መሆኑን ያመለክታል ከመጨረሻዎቹ ከ2ቱ ምዕራፎች ለወደፊት ከሚናገሩት በቀር ::

ሐ. <u>በማያቋርጥ የታሪክ ስልት፤</u> በዚህ መሠረት የሔድን እንደሆነ ደግሞ የምንረዳው ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ዘመን ጀምሮ እስከ ምጽአት ድረስ የሚሆነውን ይገልጣል ::

መ. <u>ያልተፈጸመ ትንቢት፤</u> መጽሐፍ በሙሉ ከምዕራፍ 4—22 ድረስ ያለው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ገና ያልተፈጸመ ትንቢት ያለበት 2ኛ የክርስቶስ መምጣትን ሺህ ዓመት በምድር ነግሦ መኖርን ይናገራል ::

www.ethiopianorthodox.org

3. <u>የመጽሐፉ አውነተኛነት፤</u> ይኸ መጽሐፍ በዮሐንስ ወንጌላዊ መጻፉ የታመነ ነው ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሲፉ አደርገው ጽፈው ይገኛሉና፤ ከነርሱም ውስጥ ሰማዕት ዮስቲኖስ ለትሪፎና በአደረገው ዲያሎግ ምስክሯል/ምዕ. 81 / ሔሬኔዎስም ለመናፍቃን ተቃውሞ በጻፈው ራእዩን ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደጻፈው መስክሯል/4.20፣11 30.4.5.26፣1.35.2/ :: አርጊኒስም በዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ ላይ በመጀመሪያው መጽሐፍ ላይ ተናግሯል :: ኢፖሊቶስም ስለ ክርስቶስና ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚዎች በጻፈው 36 ኛው ምዕራፍ ላይ ይኸን መጽሐፍ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደጻፈው ገልጦ ጽፏል :: እንዲሁም በሙራቶሪዩ ቀኖና ላይ ይኸ መጽሐፍ በዮሐንስ ስም ይገኛል ::

www.ethiopianorthodox.org